EthioLion

# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

# Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ነሐሴ 8 ቀን 2002 ዓ.ም.**

**አንድ የወያኔ ካድሬ አምስት አባል የመመልመል ግዴታ ተጣለበት፤**

**የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ድንገተኛ ስብሰባ ለ3 ቀናት አደረገ፤**

**ዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን የሚል ህዝብን ማደናገሪያ አዲስ ስልት አውጥቶ ህዝቡ በግዳጅ እንዲያጸድቀው ሊደረግ ነው፤**

**በአዲስ ህግ ህዝቡን እግር ከወርች ሊያስር መሆኑ ተጋለጠ**

EthioLion.com

ህዝቡ የክረምቱ ቆራ እያንዘፈዘፈው፣ የረባ እህል የሚበላው ባጣበት፣ በአግባቡ የመብራት አቅርቦት ባላገኘበት በዚህ ክረምት ወራት ወያኔ ያረጀና የመነቸከ ፖለቲካውን ሊግተው መልሶ አዲስ እቅድ ማውጣቱን ከደረሰን ጥቆማ ሊማወቅ ተቻለ።

ከቻይና ጋር አፍለኛ ፍቅር ጨምድዶ የያዘው ይሔው ዘረኛው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ባሳተመውና ለአባላቶች ባሠራጨው መፅሀፉ ላይ እንደገና ሌላ አዲስ ስልት በሚል ማውጣቱ ታውቋል።

ባወጣውና ባሰራጨው መፅሀፉ ላይ እንደገለፀው ከሆነ እስከ ዛሬ አምነውም ሆነ በኑሮ አስገዳጅነት አባልና ቀንደኛ ካድሬ የሆኑት በሙሉ እያንዳንዳቸው 5 አምስት አባሎችን ማፍራት ግዴታቸው እንደሆነና ይህን ማድረግ ያልቻለ የአቅም ማነስ እንዳለበት አጉልቶ የሚያሳይና እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል የሚል መሆኑን ገልፆ ከመስከረም ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ አትቷል።

ወያኔ ባወጣውና ለአባላቶቹ በምስጢር ባሠራጨው በዚሁ መፅሀፉ አማካኝነት እንደባለፈው ከሆነ በመጪው አምስት አመት ከህዝቡ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ መስራት ይገባናል ያለ ቢሆንም ከከዚህ ቀደሙ በበለጠ ሁኔታ ካድሬቹ ወደ ሕዝቡ ውስጥ ዘልቀውና ጠልቀው በመግባት የህዝቡን እንቅስቃሴ መሰለል እንደሚጠበቅባቸው ድፍን በሆነ መልኩ አስቀምጧል።

ከወያኔ በስተቀር ከእንግዲህ ወዲያ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለሀገሪቷ አማራጭ የሌለው መሪ ፓርቲ የሌለ መሆኑን ያወሳው የተበተነው መፅሀፍ በቀጣይ 15 ዓመታት ያለ አንዳች ጥርጥር ብቸኛ ፓርቲ ሆኖ መቀጠል እንዳለበትም አፅንኦት ሰጥቶ ገልፆል።

ለ19 የግፍና የመከራ ዓመታት በህዝብ ጫንቃ ላይ ሲያናጥር የኖረው ይሔው አረመኔ እና ዘረኛ ቡድን የእስከዛሬው አልበቃ ብሎት በአዲስ መልክ እራሱን አጠናክሮ ለሌላ 20 ዓመት በስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለውን ዕቅድ በምስጢር አሳትሞ ለአባላቱ ባሰራጨው መፅሀፍ ያሳወቀ ቢሆንም ነባርና ቀንደኛ አባላቱ እርስ በርስ በጥቅም እየተጋጩ ስልጣንና ሀላፊነታቸውን እየለቀቁ በመሆኑ ወያኔ ከውጭ ሳይሆን በራሱ ውስጥ በሚነሳ ጥያቄ እራሱን ሊንድ ይችላል የሚሉ ወገኖች በርካታ ናቸው።

በአንዲት ኢትዮጵያ ዙሪያ የተጠናከረ ለሀገር እና ለህዝብ ልዕልና ተግቶ የሚሰራ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ እስካልተፈጠረ ድረስ በወያኔ አባሎች መሀከል የተጀመረው ሽኩቻ ተስፋፍቶ ሊፈረካከስ ይችላል እንጅ ወያኔ በራሱ እና ተቃዋሚ ነን በሚሉት ተጨባጭ እውነታ ከሄድን ብዙ መስራት የሚቀር መሆኑንም ምሁራኖች እየገለፁ ናቸው።

ሌላው ቢቀር ይላሉ ምሁራኖቹ ሌላው ቢቀር በተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች መሀከል መተማመን፣ መግባባት ብሎም መደጋገፍ ሳይኖር ዘረኛውን የወያኔ ቡድን መታገልና መጣል ቀርቶ እራሳቸውን በአግባቡ ሊያቋቁሙ ይቸግራቸዋል ሲሉም አስተያየታቸውን ሲሰጡ ተደምጠዋል።

አንዳንድ የተቃዋሚ ፖለቲካ መሪ ነን ባዮች ለሆዳቸው እንጅ ለህሊናቸው. . . ለግላቸው እንጂ ለህዝቡ፣ . . . ለጉጣቸው እንጂ ለሀገራቸው የማያስቡ አርቆ ማስተዋል የተሳናቸው እንደ ጋሪ ፈረስ ግራ ቀኙን ማየት ተስኗቸው ወያኔ በቀደደላቸው ቦይ ብቻ የሚፈሱት አሜኬላች ተመንጥረው እስካልተወገዱ ድረስ ትግሉ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለው እንደማያስቡ የገለፁት እነኚሁ ምሁራኖች በተለይ በ1997ዓ.ም ህዝቡ በእጅ ያስገባውን ድል ያስነጠቁት እነ ስም

EthioLion.com

አይጠሬ የወያኔ ተለጣፊ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪች ነን ባዮች የፈጠሩት ወደር የለሽ አድርባይነት መሆኑንም ምሁራኖቹ በቁጭት ይገልፃሉ።

ወያኔ በበኩሉ በአሁኑ ወቅት የያዘውን ስልጣን የበለጠ ለማጠናከር ከመቸውም ጊዜ በላይ በወታደራዊ፣ በፌደራል ፖሊስ እና በደህንነት መዋቅሮቹ እራሱን ከማጠናከሩም ባሻገር ተማሪ የተባለውን ክፍል በገንዘብና በግዴታ እየመለመለ ባሪያ እያደረገው ይገኛል።

በዚህ መሠረት ዛሬ ወደ ዩኒቨርስቲ የሚገቡ ለጋ ወጣቶች ሳይቀር መምህራኖች ጭምር የወያኔ አባል መሆን ግዴታ የተጣለባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ እነሱም በተዋረድ ሌሎችን እያስፈራሩና እያስገደዱ እየመለመሉ ዩኒቨርስቲች  ከትምህርት ማዕከልነት ይልቅ የካድሬ ማፍሪያ (መፈልፈያ) ሆነዋል።

ከመደበኛ ትምህርት ይልቅ የፖለቲካ፣ ከቴክኒክ ይልቅ ቅስቀሳን ተምረው የሚወጡ ተማሪች በየቀበሌና ወረዳ ብሎም ዞንና ክፍለ ከተማ እየተሰባሰቡ ህዝቡን እያተራመሱ ከመሆኑም በተጨማሪ ከህዝቡ ጉሮሮ ላይ እየነጠቁ በአጭር ጊዜ ቱጃር እየሆኑ መታየታቸው ስርዓቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየነቀዘና እንደ ሸክላ ውስጥ ውስጡን እየተቦረበረ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው ተብሏል።

እነዚህኑ በሙስና የነቀዙ ፍፁም ሀገራዊ ራዕይ የሌላቸውና ሁሉን ለራሴ የሚሉ ወጠጤ አፍለኛ ካድሬችን ወደ ስልጣን ለማምጣትና አሮጌቹን ለማሽቀንጠር በሚል ለ15 ቀናት ያህል በየካምፖቹና ማሰልጠኛ ቦታች እንደ ሰርዲን ታሽጉባቸው የመለስን መፅሀፍ እንዲሸመድዱ እየተደረገ ሲሆን በቅርቡ ተመርቀው ከመስከረም ወደ መጨረሻ ጀምሮ ስልጣን እንደሚሰጣቸው ይጠበቃል።

በአማራ ህዝብ ስም በስልጣን ማማ ላይ ተቀምጠው ከነበሩት ኦሮሞው አዲሱ ለገሠ፣ ኤርትራዊው በረከት ስምኦን፣ ጋሞው ተፈራ ዋልዋ እንዲሁም ወላዋዩ ታደሰ ካሣ (ጥንቅሹ) በመጪው መስከረም ወር ላይ የሚሰናበቱ መሆኑን ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጠቁመው በትግሬ ህዝብ ስም ተጉልተው በህዝቡ ላይ ሲቀልዱ የነበሩት ስዩም መስፍን፣ አርከበ እቁባይ፣ ፀጋዬ በርሔ፣ አባዲ ዘሙ፣ ቴድሮስ ሀጉስ በጡረታ እንደሚገለሉ ምንጮቹ ያላቸውን መረጃ ዋቢ በማድረግ ገልፀዋል።

እዚያና እዚህ በሁለት እግሩ እንደልቡ እየረገጠ ያለው የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ የራሴ ናቸው የሚላቸውን ቀስ በቀስ እየመታ ካባረረ በሁዋላ ሳይጠሩዋቸው አቤት ሳይልኳቸው ወደየት እያለ እሱ ፊት ለመቅረብ የሚጋፉትን ትርኪ ምርኪ ግለሰቦች ሰብስቦ ለቀጣይ አምስት አመት ስልጣኑን ብቻውን ይዞ ለመቀጠል የሚያስችለውን መተማመኛ በእጁ ማስገባቱን ከወዲሁ ሙሉ ለሙሉ አረጋግጧል።

EthioLion.com

EthioLion

በተያያዘ ዜና ለ3 ቀናት የቆየ ድንገተኛ እና አስቸኳይ ስብሰባ የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ማድረጉ ታወቋል:: ዓርብ ሐምሌ 30 ቀን 2002ዓ.ም ጀምሮ እስከ እሁድ ነሐሴ 2 ቀን 2002ዓ.ም ድረስ በዘለቀው ድንገተኛ ስብሰባ ላይ ለቀጣይ አምስት አመት ምን መደረግ አለበት በሚል በህዝቡ ላይ እና በተለይ በነጋዴው ላይ ማጥበቂያ ማነቆ ለማበጀት ሲዶልቱ እንደሰነበቱ ከደረሰን ዜና ማወቅ ችለናል::

በመለስ ዜናዊ እና በአዲሱ ለገሠ መድረክ መሪነት በዚያው በአራት ኪሎ ቤተ መንግስት መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ 36 ብቻ ሆነው ሲመክሩ የሰነበቱት የወያኔ ስራ አስፈፃሚች በቀጣዩ ህዝቡን የማሳመን ስራ እንዲሠራና ነጋዴውን ህብረተሰብ ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር እንደሚገባ ተማምነው መውጣታቸው ታውቋል::

በተለያዩ ጊዜያት በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ የሚደረጉትን እንቅስቃሴች የገንዘብ ድጋፍ እያደረገ ያለውና ወደፊትም ሊያደርግ የሚችለው የንግዱ ማህበረሰብ በመሆኑ ይህን ድርጊቱን ለማስቆም ማግባባትና በቁጥጥር ስር ማዋል የ5 ዓመቱ ዋነኛ ግንባር ቀደም ተግባር መሆኑን የገለፁት የወያኔ ስራ አስፈፃሚች ህዝቡንም በተዋረድ እንዳይላወስ የተለያዩ ዘዴች ተፈጥረው መሰራት አለበት ተብሎ አቋም እንደተወሰደ ተገልፆል::

ግምገማ ወይም ተሀድሶ እጅግ አመርቂ ውጤት አስገኝቷል ያለው ይሄው የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በየጊዜው በራሱ ውስጥ የሚያደርገው ምንጠራና ማባረር ዘመቻ የእነሱን ሀሳብ ያልተቀበሉትን ሁሉ እንደልባቸው አንገት የሚያስደፉበት ስልት በመሆኑ ውጤታማ ነው በማለት እርስ በርስ ሲሞከሻሹና ሲወዳደሱ የሰነበቱ መሆኑም ለማወቅ ተችሏል::

በተለይ ግንባር ቀደም የሆኑትን መያዝ (አባል ማድረግ) ብለው ከገለፁት ከንግዱ ማህበረሰብ እና ታዋቂ የየከተማው ነዋሪች በተጨማሪ ታዋቂ ናቸው የተባሉ ምሁራኖችን መመልመል ግዴታ እንደሆነ ያተተው የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ሀገሪቱ ካለእኛ ሀገር አትሆንም እስከማለት ድረስ በስብሰባው ላይ እያነሱ እርስ በራስ ሲደጋገፉ እንደነበረም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሏል::

በመጨረሻም በቀጣዩ መስከረም ወር ለሚደረገው 8ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚረዱ እንቅስቃሴችን ለማድረግ ኮሚቴ ይሰየም በማለት የተሰየመ ሲሆን፣ የስልጣን መተካካቱንም ቢሆን ለጠላት ክፍተት በማይሰጥ መልኩ እንደሚጀመር ገልፆል::

በዚህ ስብሰባ ላይ ዋነኛ አጀንዳ የተደረገው አብይ ጉዳይ ከ2003 እስከ 2007 ለአምስት አመታት ለአገዛዛቸው የሚረዳ ስልት ተነድፎ ወደ ህዝቡ ውስጥ እንዲሰርፅ ለማድረግ ያመች ዘንድ ስራው እንዲጀመር የተወሰነ ሲሆን፣ እሁድ ዕለት የስራ አስፈፃሚው ስብሰባ ተጠናቆ ሠኞ ዕለት በየክልል ከተሞቹ ስራ አስፈፃሚ የተባሉ የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ተበትነው ግልገል ሹማምንቱን ማጥመቅ መጀመራቸው ታውቋል::

EthioLion.com

በዚህም መሠረት የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ያወጣው ህዝብን ማደናገሪያ አዲስ ስልት «የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን» በሚል መሆኑን ያጋለጠው የደረሰን ጥቆማ በዚሁ ኘሮግራም ሁሉም የሀገሪቱ ህዝቦች በተዋረድ እንዲያውቁት ከተደረገ በሁዋላ ህግ ሆኖ እንደሚወጣም ጥቆማው አጋልጧል፡፡

የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የተባለው አዲስ የወያኔ ጠልፎ መጣያ ስልቱ ህዝቦች በገዛ ፈቃዳቸው የሚያደርጉት አንዳችም እንቅስቃሴ እንዳይኖርና እንደበታቸው ተለጉሞ፣ አይናቸው ተጋርዶ እንዲጓዙ በማድረግ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ይህንንም ዕቅድ እንደሌላው ጊዜ ሁሉ የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ብቻውን ያዘጋጀው መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አጋልጧል፡፡

በቀጣይ አምስት አመት በመላ ሀገሪቱ ርሀብ ይጠፋል. . . ስራ ተፈጥሮ ስራ አጥ ጭራሽ ይጠፋል. . . የመብራት ኃይል ማመንጨት ኃይላችን ወደ 10 ሺህ ሜጋ ዋት ከፍ ይላል. . . ፈጣን ዕድገት ያስመዘገበች ሀገር እንደመሆንዋ በቀጣይም እጅግ ፈጣን እድገት ታስመዘግባለች. . . የሚሉ ቃላቶች እና እንቶ ፈንቶ የበዛባቸው አረፍተ ነገሮች ተደራርተው የተሰጡዋቸው የወያኔ ስራ አስፈፃሚች የተባሉትን እንደ ገደል ማሚቱ ለማስተጋባት በየክልል የተበታተኑ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

እሁድ ምሽት ነሐሴ 2 ቀን 2002ዓ.ም የስራ አስፈፃሚው ስብሰባ ተጠናቆ ሰኞ ነሐሴ 3 ቀን 2002ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሠዓት በየተመደቡበት ክልል ከተሞች የተገኙት እነዚህ የመለስ ተላላኪ ግለሰቦች ለራሳቸው የተነገራቸው ሀሳብ እና የተሰጣቸው ግዳጅ ሳይገባቸው ግልገል ሹማምንቱን ለማስተማር የወረዱ ሲሆን እዚያም ደርሰው ፈታኝ የሆነ ችግር እንደገጠማቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

የወያኔ ቡድን ሰሞኑን አዲስ አወጣሁ ባለው እቅድ ላይ «ኢንዱስትሪና ግብርናው በእጥፍ ያድጋል...... ማህበራዊ እንቅስቃሴው ይጎለብታል...... የመንገድ ግንባታው 64 ሺህ ኪሎ ሜትር ይደርሳል..... የባቡር ሀዲድ መስመር ዝርጋታ እጅግ በተፋጠነ ሁኔታ ከድሬዳዋ ጅቡቲ፤ከድሬዳዋ መቀሌ እንዲሁም ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ይካሄዳል...... መብራት አሁን ካለው እጅግ በላቀ ሁኔታ 10 ሺ ሜጋ ዋት እንዲደርስ ይደረጋ.......በ2007 ዓ.ም 1 ሚሊዮን የዩኒቨርስቲ ተማሪች ካምፓስ ይገባሉ ........የህክምና ተቋዋሞች እስከ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ድረስ ይዘልቃሉ....... ስንዴ መለመለን ያከትማል......» በሚል በበሬ ወለደ ባረጀና ባፈጀ የውሸት ፕሮፓጋንዳ ህዝቡን ለማታለል እና ለማጃጃል የሚያስችለውን ያወጣ ሲሆን እነሱ በተጉዋዳኝ የጀመሩትን ህዝብን ከህዝብ ማጋጨት እና ሀገርን የማፈራረስ ተግባራቸውን ሊቀጥሉ መዘጋጀታቸውን ያጋለጡት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይህን እቅድ ህዝቡ እንዲያውቀው ተደርጎ መስከረም ለሚጀምረው አዲሱ የይስሙላ ምክር ቤት ገብቶ እንዲፀድቅ እና ህዝቡም ለዚሁ

መርህ ግብር ተገዢ እንዲሆን ከመገደዱም በተጨማሪ ለዚህ ህግ የማይገዛ ከሆነ ለእስር እና ለተለያዩ ቅጣቶች እንደሚዳረግ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በተለይ ድሬዳዋ እና መቀሌ በተደረጉ በዚሁ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በሚለው አዲስ የወያኔ የቆረጣ ስልት ሙሉውን ፈጣን እድገት የሚያስመዘግቡበት አድርገው በማውራታቸው የወረዳና የዞን ካቢኔ አባላቶች አፋጣጭ ጥያቄችን በመሰንዘራቸው መልስ ለመስጠት ተቸግረው እንደነበርና የሻይ እረፍት እያሉ እየበተኑ ከመለስ ጋር በስልክ ተነጋግረው እንደገና እየሰበሰቡ ሲነግሩዋቸው እንደነበር ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል::

በመቀሌ አክሱም ሆቴል የተደረገው ስብሰባ የኦህዴዱ ካድሬ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር የሆነው ድሪባ ኩማ የተባለው ሲሆን የድሬዳዋውን ደግም መስከረም ላይ ያለቃል የተባለው የህውሀቱ አርከበ እቁባይ መሆናቸውን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በሁለቱም ከተሞች ግልገል ሹማምንቶች ያነሱት ጥያቄ በአግባቡ መልስ ሳያገኝ እንደቀረ ዘገባው አብራርቷል::

ከዚህ ቀደሞ በቀን ሦስት ጊዜ ትበላለህ የተባለ ህዝብ ሶስቱ ቀርቶ በቀን አንድ ጊዜ ማጣቱን በተግባር በማየቱ በ1997 ምላሽ የሰጠ ሲሆን አሁን ደግሞ ስራ አጥ ይጠፋል. . . ረሀብ ይወድማል. . . የአመታዊ ገቢህ ይህን ያህል ይሆናል. . . እያለን በሌለ ነገር ላይ ለመናገር ተጨባጭ የሆነ ነገርን ማሳየት ያለብን ቢሆንም አሁን የምትሉትን በመሳሳይ የዛን ጊዜውን ስህተት  በቀን ሶስት ጊዜ ትበላለህ በሉት እያላችሁን በመሆኑ አንቀበልም ስለዚህ ይህ ጉዳይ በተገቢው መንገድ እንዲጠና ሲሉም ካድሬች ባለስልጣናቱን አፋጥጠዋቸዋል ሲል ዘገባው አስረድቷል::

የወያኔው መሪ መለስ እንቅልፍ አልወስድ ሲለው በራሱ ጊዜ እየፈጠረ የሚፅፋቸውን ልብ ወለዶች ወደ ተግባራዊነት እንዲለውጡ ሲያዛቸው ይህ ከእኛ ሀገር ህዝቦች ጋር አብሮ አይሄድም ..... ተጨባጭ ለውጥ እያመጣም ብለው ሳይከራከሩ የተባሉትን ብቻ ተቀብለው ለማለት ሲሮጡ የሄዱት ስራ አስፈፃሚ ተብዬች በገዛ ካድሬ ሹማምንቶች ትችትና ዘለፋ የደረሰባቸው ከመሆኑም በላይ በመሀከላቸው መናናቁ እንደተፈጠረም ከተለያዩ የክልል ከተሞች የደረሱን ዘገባች አስረድተዋል::

የኑሮ ውድነቱ ከዕለት ወደ ዕለት እያሻቀበ ከጣራ በላይ በሆነበት በአሁኑ ሠዓት መለስ ሲመረቅን በጭፍኑ ያለ አንዳች ይሉኝታ ያወጣውንና የበተነውን ፅሁፍ ባለስልጣናቱ አምነው ወደታች እያወረዱ ቢሆንም አሁን ባለው ተጨባጭ እውነት የወያኔው ቡድን ከያዘው የዘረኝነት እና የአንድ ወገን የበላይነት መንፈስ እና የቡድን ስሜት ካልተላቀቁ ሀገሪቷም እድገት አታስመዘግብም ህዝቧም ከችግር አይላቀቅም ሲሉ አስተያየት የሰጡት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምሁራኖች ለይምሰል ብቻ የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ለውጥ አመጣን እያሉ መደስኮሩ ትርጉም የለውም  የእምቧይ ካብ ሆኖ አንድ ቀን ሁሉም ይፈርሳል ሲሉም ምሁራኖቹ ይገልፃሉ::

EthioLion.Com

EthioLion

ምሁራንን ያገለለ ስራ ከቶም ውጤት አያመጣም ያሉት እነዚሁ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምሁራኖች በግዴታ አባል ካልሆናችሁ እየተባለ ጫና መፍጠሩ ለደርግም ያልበጀ ከመሆኑም በላይ ሀገርንና ህዝብን ማታለል ነው ሲሉ ጨምረው ገልፀዋል::

ግራ የተጋባው መለስ ሰሞኑን በተከታታይ ሁለት ጊዜ ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠቱ ታውቆዋል::ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች ከፋፍሎ በሰጠው በዚሁ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ በቀጣይ ጥቅምት ወር ላይ የአሁኑ ካቢኔ ሙሉ ለሙሉ እንደሚወገድ ጠቅሶ ይህም የሆነው በመግባባት ላይ በተመሰረተ ነው ሲልም ጨምሮ ገልፆዋል::በተለይ ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ ላይ ስለ አሜሪካ ግንኙነት እና ከስዊድን ጋር ግንኙነት ስለማቋዋረጥ ማተቱም ታውቆዋል፡

EthioLion.com